የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

☎ 55 35 06, 55 17 89, 12 39 00 - Fax 251-1-55 31 55 - ✉ 882
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ - Addis Ababa, Ethiopia

ቁጥር
Ref. No. ..............................

ቀን
Date ..............................

## *ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የተሰጠ መግለጫ*

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ የኢትዮጵያን አንድነት ለማስጠበቅ የሕዝብን የስልጣን አመንጭነት፣ ባለቤትነትና ተቆጣጣሪነት ለማረጋገጥ እውነተኛ እና ሙሉ ዲሞክራሲያዊ ሥርአት ለማምጣት ሊበራላዊ ፖለቲካ ላይ የተመሠረተ ሕብረ-ብሔራዊና ትክክለኛ ሀገራዊ የፖለቲካ ፕሮግራሙን ነድፎ በሰላማዊ የትግል ስልት መታገል ከጀመረ 18 ዓመታትን አስቆጠረ።

ነገር ግን በሀገራችን ታሪክ ውስጥ ያልተለመደውን በሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ የሚረጋግጥ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ፖለቲካዊ ባሕል መሠረት ለመጣልና የመንግሥትን በሕዝብ አምንታ የመምጣት ዲሞክራሲያዊ ዘይቤ ለዘለቄታው ለማረጋገጥ ስለሚያስችል ብቻም ሳይሆን ከመጯጯህ ፖለቲካ ወር ተራ የጨቋኝነትና ተጨቋኝነት የአገዛዝ ስልት ወጥቶ እውቀት መር በሳል የመቻቻል ፖለቲካን ለማስፈን የሚያስችለው ብቸኛ መንገድ ይኸው ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ብቻ ስለሆነ ነው።

መኢአድ በተጓዘበት ሂደት በጥርጣሬና በተስፋ መቁረጥ ውስጥ የነበረውን ወገን በመቀስቀስና በማደራጀት የ1997 አይነት ሕዝባዊ ተሳትፎ እንዲፈጠር የበኩሉን አድርጓል። ይህን የመሰለ የሀገሪቱን ሁለንተናዊ የነጻነትና የልማት ጥያቄዎች ለመፍታት የሚያስችል ሕዝባዊ መነሳሳት ዳግመኛ እንዲያንሰራራና በሰላማዊ የትግል መስመሩ ለሚመጣ ለውጥ አስተማማኝ መሠረት ለመጣል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መነጋገርና መደራደር አስፈልጎ ነበር።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በታላላቅ አገሮች አምባሳደሮች የሚመራው የኢትዮጵያ አጋር ድርጅቶች /Ethiopian Partners Group/ በምርጫ ሥነ-ምግባር ደንቡ ላይ ከገዢው ፓርቲ ጋር ድርድር እንዲያደርግ ለመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ተደጋጋሚ ጥያቄ አቀረቡ። የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴም በጉዳዩ ላይ ሰፊ ውይይት አድርጎ ድርድሩ ለአገርም ሆነ ለሕዝብ እንደሚጠቅም ስለአመነበት ለጥያቄው አዎንታዊ መልስ በመስጠቱ ሁለት ወር የፈጀው ድርድር በነሐሴ ወር 2002 ዓ.ም ተጀምሮ ከሁለት ወር በኋላ ለፊራረም ችሏል።

መኢአድ በሰላማዊ ትግል አጥብቆ የሚያምን ፓርቲ ስለሆነ የድርድሩ መጀመርና ለፊርማ መብቃት በኢትዮጵያ የጥላቻ ፖለቲካን በማስወገድ ዲሞክራሲን ለማስረጽ መሠረት የጣለ ነው ብሎ ያምናል፡፡

በመሆኑም መኢአድ በቅንጅት ስም ከመሬታቸው የተፈናቀሉትን፣ ከስራ የተባረሩትን፣ ከማህበራዊ ህይወት የተገለሉትን፣ ከሀገር የተሰደዱትንና በእስር ቤት እና በክስ ላይ በፍ/ቤት በመመላስ ላይ የነበሩትን 275 አባላትና ደጋፊዎች በዝርዝር አቅርቦ በመደራደሩ በደቡብ ክልል በእስር ቤት ውስጥ የነበሩና ከእስር ቤት ውጪ በፍ/ቤት ክስ ላይ አምስት አመት ሙሉ ሲመላለሱ የነበሩትን 45 (አርባ አምስት) ሰዎች ሙሉ በሙሉ ከእስራት እና ከክስ ነፃ እንዲወጡ አድርጓል፡፡ እንዲሁም በአማራ ክልል በእስራትና ከእስር ቤት ውጪ በፍ/ቤት አምስት አመት ሙሉ ሲመላለሱ ከነበሩትና በመኢአድ ዝርዝር ከቀረቡት ውስጥ 92 (ዘጠና ሁለቱ) ሰዎች ሙሉ በሙሉ ከእስራትና ከክስ ነፃ እንዲወጡ አድርጓል፡፡ በቃሊቲ እስር ቤት ይገኙ የነበሩ 10 ግለሰቦች እንዲፈቱ አድርጓል፡፡ በአጠቃላይ በድርድሩ የተፈቱት ሰዎች ብዛት 181 /አንድ መቶ ሰማንያ አንድ/ ሲሆን የሌሎቹንና በዝርዝሩ መሠረት ጉዳያቸው በሂደት ላይ ያለውን አባላት በተመለከተ የመኢአድ አመራር ከሥር ከስሩ ጉዳያቸውን በመከታተል ላይ ይገኛል፡፡ ስለዚህ በአስቸኳይ ምላሽ እንዲሰጠውም ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ ሲሆን ውጤቱንም ለህዝባችን ይገልፃል፡፡

መኢአድ ከእስር ለተለቀቁ፣ ክሳቸው ለተሰረዘላቸው ዜጎችና ቤተሰቦቻቸው ስለ ፅናታቸው ያለውን ታላቅ አክብሮት እየገለፀ ለድርድሩ ሂደት ሙሉ ውጤታማነት ሁሉም ወገን የጋራ ጥረት እንዲያደረግ መልክዕክቱን ያስተላልፋል፡፡

በ2002 በሚደረገው ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ መኢአድ ለተወካዮችና ለክልል ም/ቤቶች የሚወዳደሩ እጩዎችን በብዙ እያቀረበ በማስመዝገብ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት ለተወካዮች ም/ቤት 380 ለክልል ም/ቤት 1205 አቅርቧል፡፡

መኢአድ በድርድሩ ከላይ የተዘረዘሩትንና ለህዝብ ጠቀሜታ ያለው ውጤት እያስመዘገበ ቢሆንም በሌላ መልኩ በኢህአዴግ በኩል የሥነ-ምግባር ደንቡን ባለማክበር በፓርቲያችን አመረሮች፣ አባሎችና ደጋፊዎች ላይ ብዙ ጉዳት እየደረሰባቸው ይገኛል፡፡

በአሁኑ ሰዓት ከድርድሩ ወዲህ ሁለት የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች ማለትም የአፋር ክልል ሰብሳቢና የመኢአድ የላዕላይ ም/ቤት አባል የሆኑት አቶ አሊ ሚራህ ያዩ እና የቤንሻንጉል ክልል ሰብሳቢና የመኢአድ የላዕላይ ም/ቤት አባል የሆኑት አቶ አዲስ ታደሰ ያለምንም ወንጀል በእስር ቤት በመማቀቅ ላይ ይገኛሉ፡፡

ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ ደብዳቤም ሆነ በአካል ቀርበን ብናስረዳም እስካሁን ድረስ የታሰሩት ሊፈቱ አልቻሉም ሌሎች አባሎችን መግደል፣ ማስፈራራት፣ ጽ/ቤት መዝጋት የመሳሰሉት ችግሮች በስፋት ቀጥለዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ምርጫው ከወዲሁ የስጋት ጥላ የጣለበት መሆኑን ልንረዳ ችለናል፡፡

ምርጫ ቦርዱን በሚመለከት በሥነ-ምግባር ደንቡ በተስማማነው መሠረት ከምርጫ ቦርዱ ሥራ አስፈፃሚዎች፣ ኃላፊዎችና ሰራተኞች መካከል በህዝብ አመኔታ የሌላቸውን

በማግለል በምትካቸው ሌሎች ገለልተኛ የሆኑትን ለመተካት ስምምነት ላይ ደርሰን ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ እልባት ሳይሰጠው በህዝብ አመኔታ የሌላቸውና ከዚህ በፊት የነበረውን ምርጫ እና ሌሎችንም አድልኦና ግፍ ሲፈፀሙ የነበሩት ተመልሰው በሥራ ላይ በመቀመጣቸው በአሁኑ ሰዓት በመላ ሀገሪቱ የተመረጡት የህዝብ ታዛቢዎች የኢህአዴግ ካድሬዎች ናቸው በማለት ያቀረብነው ማስረጃ መልስ ሳይሰጥ እንዲቀጥል በመደረጉ በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ የም/ጣቢያዎች ከፍተኛ ችግር እየገጠመን ይገኛል፡፡

ይህም በመሆኑ የምርጫው ሂደት በገዢው ፓርቲ ቁጥጥር ስር በመውደቁ፤

1. የምርጫ ህጉ ከሚፈቅደው ውጪ መዝገብ ወደየመኖሪያ ቤት ይዘው በመሄድ ምዝገባ ማካሄድ፤
2. በተለያዩ ምክንያቶች የምርጫ ጣቢያዎችን በመዝጋት ህዝቡ እንዳይመዘገብ ማሰናከል፤
3. በሰዎች መካከል ልዩነት በመፍጠር መታወቂያ የሌላቸውን ሰዎች የምርጫ ካርድ መስጠት፤
4. የምርጫ ካርድ አልቋል በማለት ተመዝጋቢዎችን መመለስ፤
5. ከምርጫ ህጉ ውጪ በመራጩ ህዝብ መካከል ልዩነት እና አድሎ በመፈፀም ለደጋፊዎቻቸው ያለ ቀበሌ መታወቂያ እንዲመዘገቡ ሲያደርጉ አይደግፉንም ብለው ለሚገምቱት እንዳይመዘገቡ ያደርጋሉ፡፡ በሌላ በኩልም መራጩ ህዝብ በሚኖርበት ቀበሌ መታወቂያ እንዲሰጠው ሲጠይቅ መከልከል፡፡
6. የገዢው ፓርቲ ወገንተኛ የሆኑት የቀበሌ ባለሥልጣኖች ቤት ለቤት እየዞሩ የመራጩን ህዝብ የተመዘገበበትን ካርድ ቁጥር እየመዘገቡ እና መራጩን እያስፈረሙ በመራጩ ህዝብ ላይ የስነ-ልቦና ጫና በማካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡

## <u>የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቅስቀሳን በተመለከተ</u>

በፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት በተደረገው ስምምነት መሠረት ፓርቲዎች በግል እና በጋራ ራሳቸውን ለህዝብ የሚያስተዋውቁ ፕሮግራም ዓርብ የካቲት 5/2002 ዓ.ም ይጀመራል፡፡ በዚህ ዕለት አምስት ወይም ስድስት የፖለቲካ ፓርቲዎች በመካከላቸው ክርክር ያደርጋሉ፡፡ የክርክሩ ርዕስም "ዲሞክራሲ፣ መድበለ ፓርቲ እና ምርጫ በኢትዮጵያ" የሚል ሲሆን አቀራረቡም ቀን ተቀድቶ ምሽት ከሁለት ሰዓት ዜና ቀጥሎ ግማሹ ሲቀርብ ቀሪው ቅዳሜ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ከዜና በኋላ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

መኢአድ ባለፉት አምስት ዓመታት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የደረሰበትን ብሶት በመገንዘብ ዛሬ በሚደረገው የመጀመሪያ ክርክር ላይ አይሳተፍም፡፡

በዓለም ላይ ካሉት ሕዝቦች የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ ሰላማዊ ነው፡፡ በመሆኑም የዛሬ አምስት ዓመት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ቅሬታቸውን ለመንግሥት በማግለፃቸው ምክንያት ከልዩ ታጣቂ በተተኮሰባቸው ጥይት ሁለት መቶ ያክል ሰላማዊ ዜጎቻችን ሕይወታቸውን አጥተዋል፡፡ በዚህ አድራጎትና ከዚያም ወዲህ መንግሥት ምንም ዓይነት የሕዝብን ዕምባ የሚያብስና ወደፊት ተስፋ ሰጭ እርምጃ ባለመውሰዱ የአዲስ አበባ ሕዝብና በመላ ሀገሪቱ ያለው ሕዝባችን ብዙ አዝኗል፡፡

ምርጫን ካሁን በኋላ ለምኔ ብሎ በማቅማማት ላይ ይገኛል። ስለዚህም መኢአድ ሕዝባችንን በልዩ ሁኔታ መቅረብ ያስፈልጋል ብሎ በጽኑ ያምናል። በመሆኑም፤

1. የክርክሩ ርዕስ የኢትዮጵያ ሕዝብ መስዋዕት የከፈሉለትን አመላካች መሆን ይገባዋል። በዚህ አንፃር መኢአድ ለምክር ቤቱ ያረቀበው ርዕስ ከአያሌ ርዕሶች ውስጥ ከአንድ ሌላ ፓርቲ ርዕስ ጋር ተቀናጅቶ እነሆ ከላይ የተመለከተው ርዕስ እንዲሆን በምክር ቤቱ ተቀባይነት አግኝቷል።

2. ሌላው መኢአድ በጽኑ የሚያምነው ክርክሩ በቀጥታ መተላለፍ እንዳለበት ነው ሆኖም ከብዙ ቀን ውይይት እና ድርድር በኋላ በኢህአዴግ አምባገናዊ ባሕሪ ምክንያት ተቀባይነትን ሳያገኝ ቀርቷል።

3. ከዚህም በተጨማሪ የሰዓት ክፍፍሉ ፍትሐዊ እንዳልሆነ መኢአድ ያምናል።

4. መኢአድ የክርክሩ አወያዮች በየርዕሰ ጉዳዩ ባለሞያዎች እንዲሆኑ በጽኑ ጠይቋል።

እነዚህ ዋና ዋና ጉዳዮች በኢህአዴግ አምባገነናዊ ባሕሪይ ተቀባይነት ባለማግኘታቸው እና ከዚህ በኋላ ስምምነት እስኪደርሱ ውይይቱን መግፋት ቢቻልም ለምርጫው የቀረው ጊዜ 100 ቀናት ብቻ በመሆኑና በዚህን ጊዜ ውስጥ ምንም ጊዜ ሳይባክን የኢትዮጵያን ሕዝብ መቀስቀስ፣ መብቱን ማሳወቅና የቀረቡለትን የፓርቲና እጩ ተወዳዳሪዎች አማራጮች ማሳወቅ ስለሚገባ የመከራከር መብቱን መኢአድ ለጊዜው ለቅቋል።

ከላይ በቀረቡት ልዩነቶችና በሌሎችም ላይ ውይይት ተደርጎ መኢአድ ወደ ክርክሩ እንደሚመለስ ተስፋ ያደርጋል።